# የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ( ኢሕአፓ)

Ethiopian People's Revolutionary Party (EPRP)


ኅዳር 27 ቀን 2001 ዓ.ም

## በወያኔ ላይ ማዕቀቡ ተጠናክሮ ይቀጥል

የመለስ ዜናዊ አገዛዝ በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ እየፈፀመ ያለው በደል ከቀን ወደ ቀን እየከፋ በመሆኑ በዚህ አገዛዝ ላይ ሁለገብ ትግሉ መጠናከር መፋፋም አለበት በሚለው አቅዋም መሰረት በወያኔ አገዛዝ የንግድ ተቋሞችና እንቅስቃሴ ላይ ዓለም አቀፍ ማዕቀቡ ሳይረግብ መቀጠል እንዳለበት ኢሕአፓ በአሁኑ ወቅት--በተለይም በዓላት እየተቃረቡ ባለበት- ዳግም ማሳሰብ ይፈልጋል።

የወያኔ አገዛዝ የታገቱ የፖለቲካ እስረኞችን ሊለቅ ቀርቶ በርካታ ዜጎችን እያፈሰ ወደ ሽዋ ሮቢትና ሌሎችም እስር ቤቶች እያስገባ ነው። በቴዎድሮስ ካሳሁን ላይም የቂም ፍርዱን አውርዶበታል። በዚያው መልክ ደግሞ በሕዝብ ቁስል ላይ ጨው እየነሰነሰ፣ በሕዝብ ችግር ላይም እየነገደና እየተሳለቀ  መሆኑ ደግሞ ተጋልጧል። ማዕቀቡ እንዳይስፋፋ በሰበብ አስባቡ ወያኔም የይፋና የስውር ደጋፊዎቹም እየሰሩ መሆናቸው ከተጋለጠ ውሎ አድሯል። ሆኖም ዛሬም ቢሆን በርካታ ዜጋ ገቢው ለወያኔ በሆነው አየር መንገድ ሲጓዝ፣ ወያኔ የሚሸጠውን ጤፍና እንጀራ ሲሸምት፣ የወያኔን ቢራና ወይን ሲጠጣ፣ በወያኔው ሜጋ ኔት የተባዙ መፅሀፍትና ቪዲዮ፥ ዲቪዲ ሲገዛ ወዘተ እየታየ ነው። በአያሌ ምግብ ቤቶች በአውሮጳ፣ በአሜሪካ ወዘተ የወያኔ ቆሳቁሶች እያቀረቡ በመሸጥ ላይ ናቸው። ለወያኔ ባደሩ ዘፋኞች ላይም ማዕቀቡ ደከም ብሏል። ይህ ደግሞ ማዕቀቡ እየላላ ወይም እየደከመ ነው ሊያሰኝ የሚችል መሆኑ መሳት የለበትም። ስለዚህም በወያኔ አገዛዝ ላይ የታወጀው የኤኮኖሚ ማዕቀብ በሁሉም መስክ ሳይረግብ መቀጠል እንዳለበት በማወቅ ማዕቀቡን እንድናጠናክር ጥሪ እናደርገላን። በንግድ የተሰማሩ ዜጎችም ይህንኑ ትግል በቆራጥነት እንዲያግዙ እናሳስባቸዋለን። ፀረ ወያኔ ነን፣ በወያኔ ላይ ማዕቀቡን እንደግፋለን እያሉ በሌላ በኩል የወያኔን ቆሳቁስ የሚሸጡ፣ የወያኔን የንግድ ተቋሞች ማስታወቂያ የሚያትሙና የሚያስተጋቡም ሰልፋቸውን በጊዜ እንዲያስተካክሉ ያስፈልጋል።

ሁሉም ዜጋ በየፊናው ለሀገሩና ለሕዝብ ይታገል!
ማዕቀቡ የወያኔን አገዛዝ የሚጎዳ እርምጃ ነውና በወያኔ ላይ ማዕቀቡ ይጠናከር!


EPRP
P.O.Box 73337
Washington DC, 20056
USA
Tel. 202-291-4217 Fax 202-291-7645

E-mail : ESPIC@aol.com

Website: www.EPRP.com

EPRP
BP 22
Bois colombes 92270
France